# ኢኮኖሚው እያደገ ነው ፤ ህዝቡ ግን በድህነት እየማቀቀ ነው !!

## የሰሞኑ ዋጋ ግሸበት ምክንያትና የአገዛዙ መፍትሄ !!

### መግቢያ

ይህ ጹሁፌ ካላፉት አስር ዐመታት ጀምሮ ኢህአዴግ በአይ ኤምኤፍ ፣ በዓለም ባንክና እንዲሁም በሌሎች ዓለም አቀፍ ተዋናይ ድርጅቶች እየተመከረ በአገራችን ምድር ተግባራዊ የሚያደርገውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኢኮኖሚያዊ ዝቀትን ብቻ ሳይሆን ህብረተሰብአዊና ባህላዊ መመሰቃቅልን እንደሚያስከትል በሰፊው እየዘረዘረ ለማቅረብ ሞክሯል። እንዲሁም ከአስር ወር በፊት አገዛዙና የዓለም ኮሚኒቲው እንደዚያ እየተመፃደቁ የሚያበስሩትን የኢኮኖሚ ዕድገት ምንነትና የህዝባችንን ዕውነተኛ ኑሮ በአርባ ገጽ በሚጠጋ ጽሁፍ ለአንባብያን አሰራጭቷል። ሌሎች ኢትዮጵያኖችም በሌላ ዘዴና አቀራረብ የኢኮኖሚውን ድቀትና የህዝባችንን መጎሳቆል ለማሳየት ሞክረዋል። ይሁንና ይህ ጸሀፊ ከሌሎች የሚለየው በአገራችን የሚታየው የኢኮኖሚ ድቀት ዛሬ ዓለምን ከሚያተራምሰው የግሎባላይዜሽን ሂደትና የኒዎ ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ በፍጹም ተነጥሎ ሊታይ እንደማይችል ነው። የብዙዎቹም ችግር የዚህን ርዕዮተ ዓለም ምንነትና የሚያመጣውን ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀልና የባህል ድቀት በፍጹም ለማየት አለመቻል ነው።

በዚህ ጸሀፊ ዕምነት ዛሬ በአገራችን ምድር የሚታየው የዋጋ ግሽበትም ሆነ አጠቃላዩ የኢኮኖሚ ሁኔታ ድቀት አገዛዙ ስልጣን ከያዘ ወዲህ እንደ አ.አ ከ1993 ዓ.ም ከአይ ኤም ኤፍና ከዓለም ባንክ ጋር በዳረገው የኢኮኖሚ ውቅር ፖሊሲ (Structural Adjustment Program) ስምምነት መሰረት ተግባራዊ እያደረገ የመጣው ፖሊሲ ውጤት ነው ። የነገሮችን ሂደት ከዚህ ለይቶ ማየትና አገዛዙ ብቻውን ተነጥሎ በሚያካሂደው ፖሊሲ ነው አገራችን እዚህ ውደቀት ላይ ልትደርስ የቻለችው ብሎ ከኒዎ ሊበራሊዝም ያልተለየ ትንተና መስጠት ዛሬ በዓለም ላይና በተለይም ደግሞ በአሜሪካ ምድር የሚካሄደውን ጠለቅ ያለ ውይይት ለመረዳት አለመሞከር ብቻ ሳይሆን አንድ ህዝብ ታሪክን እንዳይሰራ በእውቅም ሆነ ሳያውቁ ዕድሉን እንደመዝጋት ይቆጠራል። የዛሬውን የአገራችንን የኢኮኖሚ ድቀትና ህብረተሰብአዊ መተረማመስ በተራ የኢኮኖሚ ትንተና በፍጹም መረዳት አይቻ ልም። ደጋግሜ ለማሳየት እንደሞከርኩት የህብረተሰብአችንም ሆነ የአገዛዙን ትርምስና ችግር በሰፊ የስልጣኔ ቲዎሪ ፣ በተለይም ደግሞ ሜታፊዚካዊ በሆነ አቀራረብ ብቻ ነው መረዳት የሚቻለው። በሌላ አነጋገር የዛሬው ህብረተሰብአዊ ችግር የባህልና በተለይም ደግሞ አርቆ ያለማሰብ ውጤት ነው። በተጨማሪም ይህ ልዩ ህብረተሰብአዊ አወቃቀር የፈጠረው ልዩ የፖለቲካ ክስተትና ኤሊት በህዝባችን ላይ እንደዚህ ዐይነቱን ብልሹ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዲሞከርበት በማድረጉም ጭምር ነው። ይህ ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ ብቻ ነው ሰፊ ውይይት ማካሄድ የሚቻለውና ፍቱን መፍትሄ ለመስጠት ሙከራ የሚደረገው። ለዛሬው ግን በዚህ ላይ አልቆይም። ዛሬ ህዝባችንን የሚያተራመሰውን የኑሮ ውድነትና የድህነትን ምክንያት እኔ በምረዳውና ትክክል ነው ብዬ በማምነው መልክ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

### የዛሬው የዋጋ ግሸበት የነፃ ገበያው ኢኮኖሚ ፖሊሲ ውጤት ነው !!

በሰፊው ከአስር ወራት በፊት በእንግሊዘኛ ጽሁፌ ላይ እንዳመለከትኩት ፣ የዛሬ አስራ አምስት ዐመት የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ እንደመፍትሄ ሲቀርብ የታመነበት የአገራችን ውስብሰብና ጥልቅ ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በዚህ አማካይነት የሚፈታና የኢትዮጵያ ህዝቦችም የቀን ብርሃን በማየት በደስታ ይደነፍቃሉ ፤ የዓለምም ኮሙኒቲ አባል በመሆን ተከብረው ይኖራሉ የሚል እምነት ነበር። በዝርዝር እንደቀረበው ፣ የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊና የመረቀ ውጤት እንዲያመጣ ማነቆ የሚባሉ †በፍልስፍናው™ መሰረት የታመነባቸው መሰረተ ሀሳቦች ቀስ በቀስ በስራ ላይ መዋል ነበረባቸው። ይሁንና እነዚህ የገበያ ኢኮኖሚ መሳሪያዎች የሚባሉት በምንም ከአገራችን ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ አልነበሩም። መሰረተ ሀሳቦቹ በአደገና በተወሳሰበ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የፈለቁና ፣

በተለይም ከርዕዮተ ዓለም ጋር በጥብቅ የተያያዙ በመሆናቸው ለአገራችን ኢኮኖሚ ችግር እንደመፍትሄ ሊሆኑ እንደማይችሉ ግልጽ ነበር። የፖሊሲው ተግባራዊነትና ዓለም አቀፋዊ ባህርይን መያዝ ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ቀስ በቀስ እያለ የመጣውን የኃይል ሚዛን አሰላለፍ ለውጥ የሚያመለክቱ ናቸው። የአሜሪካን የኢኮኖሚ የበላይነት ከተገረሰሰበት ከ1970ዎቹ ዓመታት ጀምሮ የኬንስ ኢኮኖሚ ፖሊሲና መንግስታዊ ጣልቃ ገብነት እንዲቀንስና በኒዎ ሊበራሊዝም ፍልስፍና ላይ የሚመረኮዝ ንጹህ የገበያ ኢኮኖሚ በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ተግባራዊ መሆን አለበት በማለት የኖብል ዋጋ ተሸላሚ የሆኑት ፕሮፌሰር ሚልተን ፍሪድማን የበላይነትን በመቀዳጅት ሰበካ ይጀምራሉ። ከ1979 ዓ.ም በእንግሊዝ በሚስ ቴቸር አማካይነት ፣ ቀጥሎ ደግሞ በአሜሪካ በፕሬዚደንት ሬገን አማካይነት ኢኮኖሚው ልቅ(deregulated) እንዲሆን ይደረጋል። ፕሬዚደንት ሬገን በአማካሪያቸው በፕሮፌሰር ሚልተን ፍሪድማን እየተመከሩ በ1930ዎቹ ባንኮችን የመቆጣጠሪያ ህግ(Glass-Steagal Act) የወጣውንና ተግባራዊ የሆነውን ፖሊሲ እንዳለ በማስወገድ ለዎል ስትሪት(Wall Street) ተዋናዮች በነፃ ገበያ ስም ሀብት እንዲያካብቱ መንገዱን ያመቻቻሉ።ዛሬ በአሜሪካ የሚታየው ስር የሰደደ የኢኮኖሚ ቀውስ የዚህ የገበያን ኢኮኖሚን ልቅ የማድረግ ውጤት ነው።ይህ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በቺሌ ከፋሺዝም ጋር በመጣመር የቺካጎ ልጆች ተብለው በሚጠሩት ወጣት ኢኮኖሚስቶች አማካይነት ተግባራዊ በመሆን ጭቆናን ያስፋፋና ኢኮኖሚው በጥቂት ሰዎች ቁጥጥር ስር እንዲሆን ያደረገ ነው። ፖሊሲውን የዓለም ባንክና አይ ኤም ኤፍ እንዲቀበሉት ተደርጎ ከ1980ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ በአፍሪቃ ምድር ውስጥ ተግባራዊ በመሆን ፣ በአንድ በኩል ጥቂት ሰዎች ሀብታም ሲሆኑ በሌላ ወግን ደግሞ የድሮ አንድ ወጥ ኢኮኖሚ የባሰ ጥልቀተን እየያዘና የተስተካከለ ዕድገት እንዳይመጣ በር የዘጋ ነው። የፖሊሲውን ውጤት በአንድ የጀርመን አገር በሚወጣ ድህረ-ገጽ(www.solon-line.de) ላይ በሰፊው በአሀዝ በተደገፈ መረጃ በማሳየት በአለፈው ህዳር ወር 2007 ዓ.ም አቅርቤያለሁ። በመሆኑም ፖለሲው ተግባራዊ በሆነባቸው እንደ ጋናና ሌሎችም የአፍሪቃ አገሮች በኢንዱስትሪ ዕድገትና በቴክኖሎጂ ምጥቀት ፈንታ የአገልግሎቱ መስክ መረን በለቀቀ መልክ በማደግ ሀብት ወዳልሆነ ቦታ ላይ በመዋል ሚዛናዊ ዕድገት እንዳይመጣ ያገደ ነው። በተለይም የውጭው መስክ ልቅ በመሆኑ የብዙ አገሮች የንግድ ሚዛን ሲዛባ ፣ በዚያው መጠንም የውጭው ዕዳ እየተቆለለ እንዲመጣ ተገዷል። ለምሳሌ በጋና ለምግብ የሚሆኑ እህሎች ላይ ርብርቦሽ ከማድረግ ይልቅ ገበሬው ወደ ካካዎ ምርት ላይ እንዲሰማራ በማድረግ ለውጭ ገበያ በሚቀርበው ካካዎና የውስጥ ገበያ ላይ በሚቀርበው እህል መሀከል ከፍተኛ መዛባት ይታይ ነበር። በተጨማሪም የአገሪቱ ገበያ ለውጭ ሸቀጥ ልቅ በመሆኑ የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ልዩ የፍጆታ አጠቃቀምን እንዲለምድ በማድረግ ሀብት እንዲባክን አድርጓል። የዕዳ መጨመርና የንግድ ሚዛን መዛባት የፖሊሲው ዐይነተኛ ባህርይ በመሆን እነዚህን አገሮች የባሰ ጥገኛ እንዲሆኑ አድርጓል።

ወደ አገራችንም ስንመጣ ኢህአዴግ ፣ የውስጥና የውጭ አማካሪዎቹ ሆን ብለው የያዙት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ውስጣዊ ችግር በሰፊው አጥንቶ ለሱ የሚስማማ ፖሊሲ ከመንደፍ ይልቅ በመጣደፍና ለራሳቸው በሚያመች መንገድ ዐይናቸውን ጨፍነው የተቀበሉትን የገበያ ኢኮኖሚ ተግባራዊ ማድረግ ነበር። የፖሊሲው ተግባራዊነት እንደታየው የአገሪቱን ውስጣዊና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣውን ህብረተሰብአዊ ችግር ከመፍታት ይልቅ ፣ ጥቂት ሰዎችን ለመጥቀምና ለማደለብ ያሚያመች ነበር። ስለሆነም ድህነትንና ረሀብን ከማሰወገድ ይልቅ ፣ የባሰ ጥልቀት ኢንዲይዙና ውስብስብ በማድረግ ችግሩ ሊፈታ የማይችልበትን ሁኔታ የፈጠረ ነው። „ተመክሮ አስተምሮናል„ „ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የለም„ እየተባለ በራሳቸው አንዳንድ ተቃዋሚ ነን በሚሉ ግለሰቦች ጭምር ሳይቀር የተዘመረለት ፖሊሲ ዛሬ በገሀድ እንደሚታየው ልንወጣ የማንችለው ማጥ ውስጥ ከትቶናል። ይህ ጉዳይ በራሳቸው በጠቅላይ ሚኒስተሩ †ኒዎ ሊበራሊዝም በአፍሪቃ ምድር ለሲራ አይችልም™ በሚል ድምዳሜ ውስጥ የተደረሰበትና የመንግስታቸውን ሳይሆን ˜የራሳቸውን አስተያየት™ እንዲሰጡ የተገደዱበት ሁኔታ ነው። በመሆኑም ከአስራ ሰባት ዐመት ሙከራ በኋላ የተደረሰበት ውሳኔ ሌላ መመዘኛ(benchmark) በመፈለግ ሌላ አዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለመንደፍ የህዝብን አመለካከት ማሳሳት ነው። ይህንን በሚመለከት ባለፈው ጥቅምት ወር 2007 ዓ.ም በርሊን ከተማ የመጡት የተለያዩ የክልል ተወካዮች በሰጡት አስተያየትና በመንግስታቸው የጀርመን የኢኮኖሚ አወቃቀር እንደምሳሌ ሊወሰድ እንደሚችልና የሚቀጥለውም ርብርቦሽ በዚህ ላይ እንደሆነ ልዑካኑ ኤምባሲው ውስጥ ለተሰበሰባው ኢትዮጵያዊ አብስረዋል። በአነጋገራቸውም የኢኮኖሚ ዕድገት የሚባለው ዝም ብሎ እንደሆነና አንድ ፋብሪካ ወይም ትምህርት ቤት ከዜሮ ተነስቶ ሲተከልም ሆነ ሲሰራ እሱ የዕድገት መለኪያ እንደሆነ ያለባቸውን ችግር አሰምተዋል። በሌላ ወገን ግን ጀርመንን እንደምሳሌ ለመውሰድ ውሳኔ ሲደረስበት ከአስራሰባት ዓመታት ጀምሮ በአገራችን በአማካሪነት በየሚኒስተሩ ውስጥ የተሰገሰገው የጀርመን የተራድኦ

ደርጅት(GTZ) ሰራተኞች ምን እንደሚሰሩና ለምን የጀርመን ዐይነቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ቀደም ብሎ ተግባራዊ እንዲሆን እንዳላማከሩ ግልጽ አይደለም። ለምን አስራሰባት ዐመት እንደፈጀ መንግስትም ሆነ የተራድዖ ድርጅቱ በቂ ምክንያት ሊሰጡን አልቻሉም።

ያም ሆነ ይህ አዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንደሚያስፈልግ ውሳኔ ከተደረሰበት ወዲህ የጀርመንን ፈለግ ለመከተል የሚያስችል ፖሊሲ ተግባራዊ ሲሆን አላየንም። አሁንም እንደትላንትናው የገበያው ኢኮኖሚ ክንዋኔ በጥቂት ሰዎች ቁጥጥር ስር በመዋል በካፒታሊዝም ሎጂክ ላይ የተመሰረተ ወደ ውስጥ የአገርን ገበያ ሊያስፋፋና ሊያዳብር የሚችል በውድድር ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ ተግባራዊ ሲሆን አናይም።አሁንም እንደቀድሞው የተረፉትንና በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉትን እንደ ቴሌኮሙኒኬሽንና መብራት ሀይልና እንዲሁም የፊናንስ ተቋሙን ልቅ (liberalize) ለማድረግ ጥድፊያ ሲደረግ ነው የሚታየው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት(WTO) አባል ካልሆነች እያሉ አዲስ መጤ ወጣት ኤኮኖሚስቶች በየዜናውና በየመጽሄቱ የሚያስተጋቡበት ወቅት ነው። ከዚህ ስንነሳ የጀርመኑን የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንደምሳሌና እንደመነሻ አድርገን መውሰድ አለብን ተብሎ ሲለፈፍ ለይስሙላ እንጂ በዕውነትም ታምኖበት እንዳይደለ መረዳት ይቻላል። ደግሞስ እንደ ጀርመኑ ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ጠለቅ ያለ የፍልስፍናና የህብረተሰብ አገነባብ ታሪክ ከራስ ጋር ማዋሀድ የሚያስፈልግ ብቻ ሳይሆን ዕውነተኛ የሆነ አገር ወዳድነትንና ከበርቴያዊ ሰብአዊነትን ይጠይቃል። ለምሳሌ እነ አዳም ስሚዝን እየተቃወመ የመጣው የነ ፍሪድሪሽ ሊስትን የኢኮኖሚ ፍልስፍና ላገላበጠና ላጠና አንድን አገር እንደ ምሳሌ ከመወሰዱ በፊት በጭንቅላት ሊቋጠሩ የሚገባቸው መሰረተ-ሀሳቦች እንዳሉ ፍሪድሪሽ ሊስት ያስተምረናል። ይኸውም ከጥንቱ የግሪክ ፍልስፍና የመነጨ የሰብአዊነትን ፍልስፍናና ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊና ግለሰብአዊ ነፃነትን የሚያረጋግጥ ቲዎሪ የፖለቲካ ኢኮኖሚክሱ መሰረተ-ሀሳቦች መሆናቸውን ነው። ይህ በሌለበት ቦታ እንደጀርመን ዐይነቱን እጅግ የተወሳሰብ የአገር ግንባታ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ በፍጹም አይቻልም።

## <u>የተበላሸ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ</u>

አገዛዙ የእነ አይ ኤም ኤፍን ምክር ተቀብሎ የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲን ተግባራዊ ሲያደርግ መልክ ያለውና አገሪቱን ወደ ፊት አንድ እርምጃ እንድትጓዝ የሚያደርግ ፖሊሲ እንዳልሆነ የኢኮኖሚ ታሪክንና የምዕራብ አገሮችን ኢኮኖሚ ዕድገት ሁኔታ ላገላበጠ ወዲያውኑ ሊረዳው ይችላል። በመጀመሪያ ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን ጥድፊያ ሲደረግ በ17ኛው ክፍለ ዘመን በምዕራብ አውሮፓ ፣ በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ደግሞ በአሜሪካን ፣ ቀጥሎም በጃፓን ከ1868 ዓ.ም ጀምሮ የውስጥ ገበያን ማሳፋፋት እንደሚያሰፈልግ ግንዛቤ ውስጥ የተገባውንና ተግባራዊ የሆነውን የማኑፋክቱር ፖሊሲና የባንኩን መስክ በአዲስ መልክ በማደራጀት የኢንዱስትሪውን መስክ ፋይናንስ ማድረጊያ ለማዘጋጀት በመነሳሳትና እነዚህን አገሮች እንደምሳሌ በመውሰድ አይደለም። በመንግስት ድጋፍ መሰረትና በባንኮች ልቅ ፖሊሲ ምንም ገንዘብ ሳይኖራቸው ኢንዱሰትሪዎችን እንዲገዙ የተደረጉት ከኢህአዴግ ጋር የጠበቀ ግኑኙነት ያላቻው ግለሰቦች የያዙት ፖሊሲ በዚያው በድሮው መልክ የውስጥን ገበያ በሚያዳክም ፖሊሲ ላይ እንዲገፉበት ነው መንገድ የተለቀቀው። የአዲሱን ባለሀብታሞች ሁኔታም ለተመለከተ የካፒታለሲት መንፈስ(pioneer sprit) የሌላቸው ብቻ ሳይሆን ፣ የታያቸው እንዴት አድርገው በሸወዳ ሀብታም ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነበር። ይህ የድሮውን ዐይነት የኢንዱስትሪ ተከላ ከአዲሱ ሁኔታ ጋር በማስማማት ተግባራዊ ማድረግ አገሪቱ ያለችበትን ውስጣዊ የኢኮኖሚ ችግር የባሰ ውስብስብና ጥልቅ እንደሆን አደረገው።

የአገራችን የኢኮኖሚ ተቅዋም በአመሰራረቱ ለካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ዕድገትና ለውድድር በሚያመች መልክ የተዋቀረ አልነበረም። ለምሳሌ የፍጆት ዕቃን የሚያመርተው የኢንዱስትሪ ክፍል በሌላ ኢንዱስትሪ የተደገፈ አይደለም። በሌላ አነጋገር በካፒታሊሰት ኢኮኖሚው ውስጥ እንደሚታየው ውስጣዊና ህብረተሰብአዊ የስራ ክፍፍል የዳበረበት ኢኮኖሚ አይደለም በአገራችን ምድር ከ1950ዎቹ ዓመታት ጀምሮ የተዋቀረው። ከዚህም በላይ ይህ ዐይነቱ የተኮላሸ ኢኮኖሚ መስክ በሳይንስና በቴክኖሎጂ የተደገፈና ቀስ በቀስ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሊሸጋገር የሚያስችለው ሁኔታ በፍጹም አልተዘጋጀለትም። ከዚህ በተረፈ እንደ ካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ የተለያዩ የኢንቬስትሜንት ህጎችን በመከተል ጥልቀትንና ስፋትን እያገኘ በመሄድ የስራ መስክን ሊከፍትና የውስጥ ገበያን ሊያዳብር የሚችል የኢንዱስትሪ መስክ አይደለም በአገራችን ያለው። የኢንዱስትሪ መስክ ራሱ ለእርሻው መስክ በአንድ በኩል የምርት መሳሪያዎችን አቅራቢ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የእርሻ

ምርትን እንደ ጥሬ ሀብት ጠያቂ በመሆንና በመጠቀም ራሱ ገበያ በመሆን የገበሬውን ተሳትፎ ሊያነቃቃ የሚችል አይደለም። ከዚህ ወጣ ስንል ደግሞ በአንድ በኩል በባንኩና በኢንዱስትሪ መስክ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በባንኩና  በእርሻው መስክ የጠበቀ ግኑኝነት የለም። የባንኩ መስክ በይበልጥ ንግድንና የህንጻን ስራ ፋይናንስ የሚያደርግ እንጂ በፍጹም የኢንዱስትሪ መስክ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ እንደ ሁኔታውና እንደ አስፈላጊነቱ ካፒታል የሚያቀርብ ሆኖ የተዘጋጀ የባንክ አደረጃጀት ስርዓት አይደለም በአገራችን ሲሰራበት የቆየው። ስለዚህም የባንኩ መስክ መጫወት የሚገባውን ሚና ተግባራዊ እንዳያደርግ የታገደበት ሁኔታ በአገራችን ተፈጥሯል ማለት ይቻላል።

ስለሆነም ግልጽነተና ዐላማ የሌለው የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ገንዘብ ያላቸውንና ኢንቬስት ለማድረግ የሚፈልጉትን ሁሉ በአልባሌ ቦታ ተሰማርተው ሁኔታውን እንዲያዘበራርቁ ነው መንገዱ የተከፈተላቸው። የገበያ ኢኮኖሚው ተግባራዊ እየሆነ ከመጣ ከአስራሰባት ዓመት ጀምሮ በገሀድ የምናየው ከኢንዱስትሪ ተከላና መስፋፋት ይልቅ የንግድ መስክና እንዲሁም የአገልግሎት መስኩ ነው እየተስፋፋ የመጣው። ከህዝቡና ከአገሪቱ ፍላጎትና የዕድገት ጋር የሚመጣጠን የኢንዱስትሪ ግንባታ ማካሄድ ሲያስፈልግ በአዲስ መጤ ከበርቴዎችና በአገዛዙ የተያዘው ሙያ ብዙ ኃይልን(Energy) ፣ ካፒታልንና ለህዝቡ የሚጠቅም ውሃን በከፍተኛ ድረጃ የሚጋራ ሆቴል ቤቶችንና የመዋኛ ቦታዎች ነው በብዛት ማሰራት የተጀመረው። የትላልቅ ሆቴል ቤቶች በአንድ በኩል መሰራት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ያሉት የውሃ መቋጠሪያዎች አለመስፋፋትና አለመሻሻል በአዲስ አበባ ውስጥ የመብራትም ሆነ የውሃ እጥረትን አስከትሏል። በዚህም ምክንያት በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ በውሃ ጥማት ይሰቃያል። ይህ የሚያሳየው የአገዛዙን እርቆ አለማሰብ ብቻ ሳይሆን የሚሰሩት ስራዎች በሙሉ የህብረተሰብ ሳይንስንና የተፈጥሮን ህግ እንዲሁም ሎጂክን ተከትለው ከብዙ አንጻሮች አኳያ የማይነደፉና የሰውን ልጅ ምንነት ማዕከላዊ ቦታ ላይ ያለስቀመጡ ፖሊሲዎች ናቸው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። በሌላ ወገን ደግሞ ልቅ የሆነው የውጭ ንግድ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች በመጋፋትና በማዳከም አይ ስራቸውን እንዲያቀዘቅዙ ወይም ደግሞ እንዲዘጉ በማድረግ የስራ አጡን ቁጥር እንዲጨመር በማድረግ ሌላ ገዝቶ ሊጠቀም የማይችል የህብረተሰብ ኃይል እንዲፈራ አድርጓል ማለት ይቻላል። ከዚህ ስንነሳ አድጓል ተብሎ የሚለፈፍለት ኢኮኖሚ በቂ አዲስ የስራ መስክና የፍጆት ዕቃን ገዝቶ ሊጠቀም ለሚችል ሰራተኛ  የስራ መስክ እንዳልከፈተ ማረጋገጥ ይቻላል። የስራ መስክ ተከፈተ ቢባል አበባ በብዛት በተተከለባቸው አካባቢዎች ሲሆን ፣ በዚህ መስክ ተቀጥሮ የሚሰራው ደግሞ አስፈላጊውን ነገሮች ገዝቶ ለመጠቀም የሚያስችለው የቀን አበል ሊያገኝ የሚችል አይደለም። ከዚህ ስንነሳ ባለፉት አስራ ሰባት ዐመታት የሰፊው ህዝብ የመግዛት ኃይል እየተዳከመ የመጣ እንጂ ከፍ እያለ በመምጣቱ አይደለም የዋጋ መናር ሊታይ የቻለው። በሌላ አነጋገር ባለፉት አስራሰባት ዐመታት የኢኮኖሚው ፖሊሲ ሰራተኛንና ገቢ ሊያገኝ የሚችልን የህብረተሰብ ክፍል  ኃይል ሳይሆን ፣ ዝም ብሎ ቀኑን እየቆጠረ የሚኖርና ሲያገኝ በልቶ ሲያጣ ደግሞ ጾሙን ውሎ ጾሙን የሚያድር የህብረተሰብ ክፍል ነው የፈጠረው። ይህንን የህዝቡን የስቃይ ኑሮ ለመረዳት ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ የሚወራውን ቀልድ ማጤን ያስፈልጋል። አንድ ልጅ አባቱን አባዬ 50 ሳንቲም ስጠኝ ዛሬ ትምህርት ቤታችን አስማተኛ ሰለሚመጣና አስማት ስለሚያሳይ እሱን ማየት እፈልጋለሁ ብሎ ለአባቱ ይነግራል። አባቱ በመናደድ የምን አስማተኛ ነው ደግሞ የምታየው ፣ እኔው አስማተኛ አባትህ እዚህ እያለውልህ እያሉ እየተቆጡት ይናገራሉ። ልጁም በመገረም አባዬ ከመቼ ጀምሮ ነው አስማተኛ የሆንከው ብሎ አባቱን ይጠይቃል። ስማ ልጄ እኔ አባትህ አስማተኛ ባልሆን ኖሮ እንዴት አድርጌ ነው በዘጠና የኢትዮጵያ ብር ስድስት ልጅ ወልጄ የምቀልብና የማሳድገው ብለው ቁጭታቸውን ይነግሩታል። ይህ አነጋገር በብዙ ሚሊዬን የሚቆጠሩ እናቶቻችንና አባቶቻችንን የሚመለከት ነው። ከውጭ እየተላከለት እየታገዘ የሚኖር ካልሆነ በስተቀር አንድ ጊዜ ብቻ ምኑንም ምናምኑን እየለቃቀመ በልቶ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ቁጥር ጥቂት አይደለም። ይህንን ስንመለከት የኢኮኖሚ ዕድገት የሚባለው የጥቂት ግለሰቦች ዕድገትና መንፈላሰስ እንጂ የአብዛኛው ህዝብ የኑሮ መሻሻል እንዳልሆነ ለብዙዎቻችን አገር ወዳዶች ግልጽ ነው። ለዚህ ደግሞ የኢኮኖሚ ጠበብት መሆን አያስፈልግም። የኢትዮጵያ ሁኔታና የህዝባችን ኑሮ ህያው ምስክሮች ናቸው።

የአገዛዙ የተበላሸ የኢንዱስትሪ ፖለቲካ በዚህ ብቻ የሚገለጽ አይደለም። የሚተከሉት ኢንዱስትሪዎች በአንድ በኩል አካባቢን የሚያቆሽሹ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በአንድ አካባቢ በመከማቸት ህብረተሰባዊ መዛባትና ሀብት ከተወሰኑ አካባቢዎች እየተሚጠጡ እንዲሄድ በማድረግ ድሮ የነበረውን ልዩነት እንዲስፋፋ ያደረገ ነው። አንዳንድ ዕድገት ታየ በሚባልባቸው አካባቢዎች ደግሞ ታታሪ አስተዳዳሪዎች ተከታታይ ስራ እንዳይሰሩ በማንሳት አዲስ አበባ መጥተው ቢሮክራሲው ውስጥ እንዲታሹ በማድረግ ግልጽ የሆነ ደባ እየተሰራ ነው። በዚህ መልክ ተጀምረው የሚቀሩ ፕሮጀክቶችና ሀብት ፈሶባቸው የሚበታተኑ የስራ መስኮች ጥቂት እንዳይደሉ ይነገራል። በተጨማሪም በብዙ አካባቢዎች የሰለጠነ ኃይል

እጥረት እንዳለና ያሉትም ነጻነት ተሰምቷቸው ስራቸውን ለመስራት እንደማይችሉ ይታወቃል። ከዚህ ባሻገር አንዳንድ የተራድዖ ድርጅቶች በገጠሩ ውስጥ ፕሮጅክቶችን ሊያቋቁሙ ሲሉ ወይም ህዝብን አዲስ የስራ ባህል ሊያስተምሩ ሲፈልጉ የመንግስቱ ካድሬዎች እንቅፋት እንደሚሆኑ በገሀድ የሚታወቅ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዴት አድርጎ የአንድ አገር ኢኮኖሚ ሊያድግ ይችላል ? እንዴትስ ግለሰብአዊና ህብረተሰብአዊ ፍላጎቶች ሊሟሉ ይችላሉ ? በጣም አስቸጋሪ ነው። ግራ የገባቸው አገር ቤት እየተመላለሱ የሚመጡ ኤክስፐርቶችም ሆነ ሌሎች ኢትዮጵያውያኖች እንደሚያወሩት አገዛዙ ምን እንደሚያስብና ምን እንደሚፈልግ ማወቅ እንደሚያስቸግር ነው። አንዳንድ ጉዳዩን በደንብ የተረዱ ሰዎች እንደሚሉን አገዛዙም ሆነ በቢሮክራሲው ውስጥ የተሰገሰጉት ሰዎች ነገሮችን የሚረዱት በጭንቅላታቸው እያቆሙ እንደሆነ ነው። በሌላ አነጋገር የኢኮኖሚ ዕድገት ሲባል ግልጽ የሆነ የፍልስፍናና የሳይንስ መመሪያ እንደሌለው ብዙዎች ይናገራሉ። እንደዚሁም ህብረተሰብ የሚለው ጽንሰ-ሀሳብና እንዴትስ በመተሳሰር በዕውቅ(organic unity) እንደሚገነባ በመንግሰት ደረጃም ሆነ በሌሎች ኢንስቲቱሽኖችና በዩኒቨርሲቲውም ውስጥ የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ነው።ስለዚህም ህብረተሰቡ ካለምንም ፍልስፍና ተፈጥሮአዊ የማሰብ ኃይሉን ሳይጠቀም እየተንገዋለለ እንዲኖር የተረገመ ይመስላል።

ይህ ፍልስፍናና ህብረተሰብአዊ መሰረት የሌለው የኢንዱስትሪ ፖለቲካ ከኢህአዴግ ጥቅም ጋር በተያያዙ ወደ አስራሰባት በሚጠጉ ትላልቅ ኩባንያዎችና የንግድ መደብሮች ቁጥጥር ያለ ሲሆን ፣ በተጨማሪም ሌላው ትልቁ የኩባንያዎች ተቆጣጣሪ የአረብ አገሮች ተላላኪ የሆነው አላሙዲን በኢኪኖሚው ዕድገት ከፍተኛን ሚናን ይጫወታል። ይህ ግለሰብ ከሌሎች ከማሌዢያና ከአንዳንድ የአረብ አገር ኩባንያዎች ጋር እየተመሰጣጠረ የሚያቋቁማቸው ኩባንያዎች አገራችንን ወደ አዲስ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ውስጥ እየለወጣትም እደመጣና በተለይም የብልግና ባህል በማሰፋፋት የወጣቱን ሞራል በማበላሸት ላይ እንደሚገኝ በግልጽ ይታወቃል። ይህ በዚህ እንዳለ ኢህአዴግም ሆነ አላሙዲን ያግበሰበሱትና የሚቆጣጠሩት ሀብት ሳያንሳቸው እዚህና እዚያ ጣልቃ በመግባት በአገሪቱ ውስጥ ዕውነተኛ ውድድር እንዳይፈጠርና የቴክኖሎጂ ምጥቀት እንዳይመጣ እያገዱ ነው። በተለያዩ መስኮች ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉ ግለሰቦች አይ የኢህአዴግን ቡራኬ ማግኘት አለባቸው ፤ ካለበለዚያም በቢሮክራሲያዊ መጎሳቆል ሀሞታቸውን እንዲቆርጡ እየተደረጉ ዕውቀታቸውንና ካፒታላቸውን በስራ ላይ እንዳያውሉ በግልጽ እየታገዱ ነው። ሌሎች በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ደግሞ በማንአለኝበት ከአቅማቸው በላይ ቀረጥ እንዲከፍሉ እየተገደዱ የንግድ እንቅስቃሴያቸውን የሚዘጉ ጥቂት እንዳይደሉ በገሀድ ይታወቃል። በዚህ እጅግ በተመሰጣጠረና ተንኮል በተሞላበት እንዲሁም ደግሞ የጥቂት ግሰለቦች የማንአለኝበት በሰፈነበት አገር ዕውነተኛ በውድድር ላይ የተመሰረተና ቀስ በቀስም አገሪቱን አዳርሶ የኢኮኖሚ ዕድገትን ሊያመጣ የሚችል በመንግስት የሚደገፍ የካፒታሊስት ወይም የገበያ ኢኮኖሚ መመስረት በፍጹም አይቻልም። የዛሬው አገዛዝ በአላሙዲንና በውጪ ኩባንያዎች እየታገዘ የሚያካሂደው ጥቂት ሰዎችን ብቻ የሚያደልብ የገበያ ኢኮኖሚ ቶሎ ካልተገታ በስተቀር አገሪቱን ወደ ማይሆን አቅጣጫ በመምራት ልንወጣ የማንችለው ማጥ ውስጥ እንደሚከተን ከአሁኑ መታወቅ አለበት። ከዚህ ስንነሳ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ስለገበያ ኢኮኖሚና የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም ስለህብረተሰብ ግንባታ ያላቸውን አመለካከት በግልጽ እየተነተኑ ማስቀመጥና ማስተማር አለባቸው። ስለዚህም ዛሬ በአገራችን የሚታየው በአኮኖሚ ዕድገት ስም ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀልና የህዝቡ ድህነት መንግስት አስራሰባት ዐመት ያህል ከተከተለው የኒዎ ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተነጥሎ ሊታይ እንደማይችል በግልጽ መቀመጥ አለበት። ይህ ሲሆን ብቻ ማን ለምን እንደሚታገልና አገር ወዳዱን ከሸፍጠኛው ነጥሎ ማየት ይቻላል።

## <u>የተበላሸ የእርሻ ፖሊሲ</u>

ኢህዴግ ስልጣን ከያዘ ከጥቂት ወራት በኋላ ባሰራጨው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለእርሻው መስክ ልዩ አትኩሮ እንደሚሰጥ አረጋግጧል። ይሁንና የአይ ኤም ኤፍን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከተቀበለ ወዲህና በራሱ ውስጣዊ ባህርይ ምክንያት የተነሳ የእርሻው መስክ የተገባለትን ቃል ኪዳን ሊያገኝ አልቻለም። በመሆኑም ኤህአዴግ ስልጣን ከያዘ ወዲህ አገሪቱ በረሀብም ሆነ በእህል እጥረት ሁለቴም ሆነ ከሶስት በላይ ተጋልጣለች። በየቦታው ገበሬውን ማመሰቃል የተወስደውን የእልክ ፖለቲካ ትተን ፣ በተለይም በጎንደርና በጎጃም ገበሬውን እርስ በራስ ለማጣላት የተወሰደውን እርኩስ ተግባር ወደ ጎን ትተን ፣ አዲስ መንግስት ስልጣን ሲይዝ ማድረግ የሚገባውን አንድን ህዝብ በምግብ እርግጠኝነት እንዲሰማው

ማድረግና ምግብ በጥራትም ሆነ በተለያየ መልክ ማቅረብ የሚገባውን ኃላፊነት የኢህአዴግ መንግስት በፈጹም ሊወጣ አልቻለም።

እንደሚታወቀው 70% የሚሆነው የኢትዮጵያ መሬት ለእርሻ የሚያገለግል ሲሆን ከዚህ ውስጥ 11% ብቻ ለእርሻ ይውላል። 85% የሚሆነው ህዝብ በገጠር ውስጥ ሲኖር ሙያው ከእርሻና እርሻን ከመሳሰሉ ተግባራት ጋር የታያያዘ ነው። አብዛኛው ህዝብ እጅግ ወደ ኋላ በቀረ የአስተራረስ ዘዴ ሲጠቀም ፣ ከአንድ ሄክታር ባነሰ መሬት የሚያገኘው ምርት ከእጅ ወደ አፍ የማያለፍ እንጂ በየጊዜው በበቂው አምርቶ የተትረፈረፈውን ገበያ ላይ አውጥቶ የሚሸጥ አይደለም። አብዛኛው እርሻ በዝናብ የሚመካ እንጂ እዚህና እዚያ ትናንሽ ተፋሳሽ ውሃ የሚያስተላልፍ ቦይና እየተጠለፈ መሬቱን ሊያርስ የሚችል የውሃ አጠቃቀም ዘዴ በፍጹም አልተለመደም። ኢትዮጵያ በውሃ ክምችትና በወንዝ ብዛት በዓለም ወስጥ አምስተኛ ቦታን መያዟ ሲታወቅ የተያዘው የግዴታ ትላልቅ ወንዞች ካልተገደቡና እነሱ ለእርሻ ካልዋሉ ምርታማነትን ለመጨመር እንደማይቻል ተደርጎ ነው የሚነገረን። ለምሳሌ በምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ትላልቅ ወንዞችን እየገደቡ ለመስኖ የሚጠቀም አገር አለ ብሎ መናገር አይቻልም። በብዙ የአውሮፓ አገሮች የመሬት አያያዝና ደንን የመጠበቅና የመንከባከብ ባህል የዳበረ በመሆኑ የዝናብ እጦት የሚታይባቸው ጊዜያት በጣም የተወሰኑ ናቸው።በአገራችን የመሬትን አያያዝና የዛፍ ተከላን እንደ አካባቢው ሁኔታ እያጠና ገበሬውን የሚያስተምር ኢንስቲቱሽን በየቦታው ስላልተስፋፋ ፣ ገበሬው በየጊዜው በዝናብ እጦት የእርሻ ተግባሩን ማካሄድ አይችልም። ይህ ሁኔታ የመሬቱን ልምላሜነትና ምርታማነት እንደሚቀንሰው የታወቀ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም በደን ጭፍጨፋ የተነሳ መሬቱ ለነፋስና አልፎ አልፎ ለሚዘንብ ኃይለኛ ዝናብ ስለሚጋለጥ የመሬቱ ለምለማ ክፍል እንዲታጠብ ሆኗል። በዚህ ምክንያት ገበያ ላይ ወጥቶ የሚሸጠው እህል ገበሬው ለራሱ ከሚያመርተው በመቀነስ ሌሎች ነገሮችን ገዝቶ ለመጠቀም ገንዘብ ስለሚያሰፈልገው ነው እንጂ እንደሚባለው ትርፍ ምርት በማምረቱ አይደለም። በዚህም ምክናያትና በመሬቱ ጥበትም ሆነ መሬቱ በተደጋጋሚ ስለሚታረስ የሚሰጠው ምርት እየቀነሰ በመምጣቱ አገሪቱ ከዐመት ወደ ዐመት ህዝቡን አንቆ በያዘ የእህል እጥረት ውስጥ እንድትወድቅ እንደተደረገ የማይታበል ሀቅ ነው።

የገበያው ኢኮኖሚ ተግባራዊ እየሆነ ከመጣ ወዲህ ፣ በእነ ዓለም ባንክ አማካሪነት ትናንሽ ገበሬዎችን መርዳት በሚል ገበሬውን በማሰገድድ ገንዘብ እንዲበደርና ማዳበሪያ እየገዛ እንዲያርስ የተደረገው ገበሬ ምርቱን ለጊዜው ቢያሳድግም ሁኔታው በዚያ ሊቀጥል አልቻለም። ዘርንና ማዳበሪያን በየዐመቱ ገዝቶ መጠቀም ያልቻለው ገበሬ የግዴታ የምርቱን ተግባር እንዲያቀዘቅዝ ተገዷል። ምክንያቱም ማዳበሪያ የለመደው መሬት በየዐመቱ ማዳበሪያና የተባይ ማጥፊያ ሲነሰነስበት ብቻ ነው የተሻለ ውጤት ሊሰጥ የሚችለው። በሌላ ወገን የመሬቱ ይዘት ሳይጠና ማዳበሪያው ስለሚነሰነስ መሬቱ የሚገባውን ውጤት ለሲጥ አይችልም። በተጨማሪም በጥቅም ላይ ሊውል ያልቻለው ማዳበሪያና የተባይ ማጥፊያ ካለምንም ደንታ በአንዳንድ ቦታዎች በመከማቸቱ ብዙ ቀውስ እንዳስከተለ ይታወቃል። ይህ በእንዲህ እንዳለና አንድ ሰሞን ገበሬው በብዛት አመረተ ተብሎ ገበያ ላይ በትከሻውና በአህያ ይዞ የመጣውን እህል በተመጣጣኝ ዋጋ ሊሸጥ ያልቻለበት ሁኔታ እንደተፈጠረ ይታወቃል። የአገሪቱ ገበያ በድጎማ ለሚመረተው የአውሮፓው አንድነትና የአሜሪካ ስንዴና በቆሎ ክፍት በመሆኑ ገበሬው በፍጹም ሊወዳደር እንዳልቻለና በብስጭት እህሉን እየደፋ እንደተመለሰ የሚታወቅ ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እንደዚሁ በዓለም ባንክ ገፋፊነትና ብድር ሰጪነት አገሪቱ እንደዚያ የእህል ምርት በብዛት ሲያስፈልጋት የቡናን ተከላ ማስፋፋት የተጀመረው ፖሊሲ የገበሬውን አመለካከት ሊያዛንፍና ቶሎ ቶሎ ቡና ሸጦ ገንዘብ ወደ ሚያገኝበት መስክ ላይ እንዲሰመራ ተገዷል። ይህ የሆነው ደግሞ ቬትናም በቡና ምርት እየቀደመችና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሁለተኛ ቦታን እየያዘች በመጣችበት ወቅት ነው። ቬትናምም በዓለም ባንክ ምክር ነው በቡና ምርት ላይ እንድትሰማራ የተገደደችው ። ይህ ሁኔታና በዓለም ገበያ ላይ የቡና ዋጋ ወደ ታች ማሽቆልቆል የኢትየጵያ ገበሬ የጠበቀውን ገበያና ገቢ እንዲያገኝ አላስቻለውም። በዚህ የተበሳጨው ገበሬ ቡናውን እየጨፈጨፈ ወደ ጨአት ተከላ እንደተሰማራ ይታወቃል። ይህንን ሁኔታ ስንመለከት የኢህአዴግ መንግስትና አማካሪዎቹ አንድ በደንብ የተጠና አገሪቱን ከእህል ተመጽዋችነት የሚያላቅቃት የአጭር ጊዜም ሆነ የረጅም ጊዜ ዕቅድ እንደሌላቸው እንገነዘባለን። በዚህ እጅግ በተመሰቃቀለና የአገርን ዕድገትና ገበያ በሚጎዳ የእርሻ ፖሊሲ እንዴት አድርጎ ገበሬው እርግጠኝነት ተሰምቶት ሊያርስ ይችላል? ምርቱንስ እንዴት አድርጎ ሊጨምርና በአንድ በኩል ለበላተኛው እያቀረበ በሌላ ወገን ደግሞ በቂ ገቢ እያገኘ ኑሮውን ሊያሻሽል ይችላል ?

ይህ በእንደዚህ እንዳለ ከመንግስትና ከካድሬዎቹ የሚሰጡን ማረጋገጫዎች የሚከተሉት ፖሊሲ በእርሻ ላይ የተመሰረተ(agricultural lead

industrialization policy) እንደሆነ ነው። ይህ በአንዳንድ ኢኮኖሚስቶች የሚሰጥ ትንተና ብዙ የሶስተኛው ዓለም ፖሊሲ አውጭዎችን እንዳሳሳተ ይታወቃል። የእርሻን ምርታማነት ለማሳደግ የግዴታ የእርሻ መሳሪያዎችን እያመረተ የሚያቀርብ የኢንዱስትሪ ፖለቲካ ያስፈልጋል። ከታሪክ አንጻር የሰው ልጅ ራሱን ለመመገብ ሲል በአደን ፣ ፍሬ ፍሬ በመልቀምና በኋላ ደግሞ በእርሻ ሙያ ላይ ቢሰማርም ምርትን እያሳደገ ሊመጣ የቻለው የግዴታ አዳዲስ ማረሻዎችን እየፈጠረ ከመጣ ወዲህ ነው። በሌላ አነጋገር የግዴታ ተጨማሪ ምርት አምርቶና እሱን ሸጦ ካፒታል ለማከማቸትና እንደገና ኢንቬስት ለማድረግ የግዴታ የማሺን ኢንዱስትሪውና የእርሻ መስኩ አንድ ላይ ተደጋግፈው መሄድ አለባቸው። ከዚህ ስንነሳ በኢንዱስትሪው መስክ መሰረታዊ ለውጥ እስካለተደረገ ድረስ የእርሻ መስኩ ብቻውን በራሱ የሚያመጣው ውጤት የለም ማለት ነው። ከዚህ ወጣ ስንል ፣ ሰሞኑን በአገዛዙ የተያዘው ፊሊፕ ለመኪና ነዳጅ የሚሆን ሰብልና ዘይት ሊሰጥ የሚችል የፓልም ዛፍና ልዩ ዐይነት ሳር በመትከል ላይ እንደሆነ እንሰማለን። ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ አላሙዲንና አንድ የማሌዢያ ኩባንያ እንደተስማሙ ይታወቃል። የእስራኤልና የአሜሪካን ኩባንያዎችም ፊለጉን እየተከተሉ ነው። ፕሮጀክቱ በመጀመሪያ በቤኔሻጉል ክልል ሲካሄድ ወደ ፊት ስድስት ክፍለሀገራትን እንሚያዳርስ ታምኖበታል። ይህ በዓለም አቀፍ ኩባንያዎች አነሳሽነት የሚካሄድና ሊካሄድ የታቀደው የባዮ ዲዝል ምርት የእርሻ መሬትን እንደሚጋራና ወደ ፊት የታቀደ የእህል እጥረት እንደሚያስከትል ከአሁኑ መታወቅ አለበት። ይህ የባዮ ዲዝልን ለማምረት የተጀመረው ዕቅድ እየተስፋፋ ከሄደ ብዙ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንደሚያወድምና ወደፊት ለከፍተኛ ውሃ እጥረት ምክንያት እንደሚሆን ብዙ ኤክስፐርቶች ይናገራሉ። በዚህም ምክንያት የአየርን መመረዝ ይቀንሳል የተባለለት የባዮ ዲዝል ዕቅድ በብዙ እጥፍ ራሱ የባሰ ጠንቅ እንደሚያመጣ እነዚህ ኤክስፐርቶች ያረጋግጣሉ። በተጨማሪም ብራዚልና ሌሎች የላቲን አሜሪካ አገሮች እንደሚታየው ሰፊው ገበሬ ወደ አዲስ የባርነት ስራ በመሰማራት ዕውነተኛ ነፃነቱን እንደሚገፈፍ ግልጽ ነው። ከዚህ የባዮ ዲዝል ዕቅድ በስተጀርባ ትላልቅ የነዳጅ አጣሪዎችና ኢንቬስትሜንት ባንኮች ሲካፈሉበት ፣ ዕቅዱ አፍሪቃንና ላቲን አሜሪካንን ወደ አዲስ ጥሬ ሀብት አምራችነት ለመለወጥ የተወጠነ ሴራ እንደሆነ ጥናቶቹ ያመለክታሉ። ከዚህ ስንነሳ በአገራችን የሚታየው ሸር ጉድ በፍጥነት እንዲገታ ሁሉም በያለበት ተቃውሞውን ማሰማት አለበት። ከዚህ አልፈን በብዛት እየተስፋፋ የመጣውን የአበባ ተክላ ስንመለከት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝንና ለእህል እርሻ የሚያገለግለው መሬት መርዝ እየተነሰነሰበት ወደፊት ምንም ፍሬ ለሲጥ ወደ ማይችልበት ሁኔታ እተለወጠ ነው። በዚህ መስክ የተሰማሩ ገበሬዎችም እንሚሞቱና በበሽታ እንደሚሰቃዩ በቦታው ተግኝተው ትምህርት የሚሰጡ ኢትዮጵውያን ይናገራሉ። ባጭሩ የአገራችን ጉድ እንደዚህ ነው።

ይሁንና ይህ እጅግ አስቸጋሪና የመንግስት ጨቆናና የተመሰጣጠረ ፖሊሲ እያለ ትንናሹ ገበሬ አብዛኛውን ህዝብ ይመግባል። በአገራችን ሊታረስ የማይችል የእህል ዐይነት እንደሌለ ይታወቃል። የተለያዩ የስንዴ ዐይነቶች ፣ገብስና አጃ ፣ማሽላና ዘንጋዳ ፣ጤፍ ፣ በቆሎ ፣ ባቄላና አተር እንዲሁም ሽንቡራ ፣ በተጨማሪም ልዩ ልዩ ፍራፍሬዎችና የቅባት እህሎች በብዛት አምርቶ በጥሬ ሆነ በፋብሪካ መልክ እየፈጩ ለተመጋቢው ህዝብ ሊቀርብ የሚችልበት አገር ነው። ከዚህ በተረፈ ድንች ፣ ጎደሬና ወጭኖ እንዲሁም የስኳር ድንች በብዛት ሊመረትባቸው የምትችል አገር ነች። በአገራችን ያለው ችግር በአንድ በኩል ከትውልድ ወደ ትውልድ ተያይዞ የመጣ ነገሮችን ችላ ብሎ የማለፍ ባህል አለ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኤሊቱና መንግስት ክህዝቡ የስልጣኔ ፍላጎትና የታሪክን ኃላፊነት ከመቀበል ጋር አንድ ላይ ሊጓዙ አልቻሉም። ከአሜሪካን የተወሰደ የኤክስቴንሽን አሰራር ባህል የኢትዮጵያን ገበሬ አፈናቀለው እንጂ አስተራረሱን እንዲያሻሽልና የመሬቱን አያያዝ በማሳመር አጠቀላይ በገጠርና በከተማ መሀከል ሊደጋገፍ የሚችልን ልዩ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲያመጣ አላስቻለውም። ስለዚህም በአገራችን ውስጥ በእርሻው መስክ መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ ከተፈለገ አነስተኛና ማዕከለኛ ገበሬዎች ሊዳብሩበትና ተደጋገፈው አዲስ የአስተራረስ ዘዴ ሊፈጥሩ የሚችሉበት ሁኔታ በሁሉም መስክ መዘጋጀት አለበት። በተጨማሪ ዛሬ በዓለም አቀፍ በከፍተኛ ደረጃ በጥቂት ኤሊቶችና በዓለም አቀፍ ኩባንያዎች አማካይነት ተፈጥሮን የማናጋትና የአስተራረስን ባህል የሚያፈራርስ ፖሊሲ በየአገሩ ተግባራዊ ስለሚሆን ወደ አገራችንም እየተዛመተ በመምጣት የዛሬውንንም ሆነ የወደፊቱን ትውልድ የአኗኗር ስልትና የምግብ አጠቃቀም ባህል ስለሚያዘበራርቅና ጤንነቱንም ስለሚያቃውስ ካሁኑ ካልታሰበበት አገራችን ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ እንደምትወድቅ ከአሁኑ መተንበይ ይቻላል። ስለዚህም የእርሻን መስኩን ብቻ ሳይሆን ህብረተሰብአችን ረጋ ባለ መልክ የስልጣኔ ባለቤት ሊሆን የሚችልብትን መንገድ በየጊዜው ማጥናትና አደጋዎችን መጠቆም የምሁር ኃላፊነት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

# የዋጋ ግሸበት ምክንያት

ዛሬ በተለይም በከተማው ውስጥ የሚኖረውን ህዝብ ከጨው ውድነት ጀምሮ እስከ በርበሬና ሽንኩርት እንዲሁም እህል ውድነት ድረስ  እንዳስመረረው ይታወቃል። የኑሮ ውድነት እንደዚህ አሁን ዐይኑን አፍጦ ጥርሱን አግጦ ይውጣ እንጂ ይህ ጉዳይ ከሁለት ዐመት በላይ እንደሆነው ይታወቃል። በመንግስት በኩል በቂ ምርት እንዳለ ፣ ይሁንና የገበሬው የመሸጥ ባህልና የነጋዴው ጊዜን እየጠበቀ መሸጥ ለዋጋው ውድነት መባባስ እንደምክንያት ይሰጣሉ። እነዚህ ትንሽ ዕውነት ያዘሉ ቢመስሉም ሁኔታዎች ግን ላይ ከተሰጡት ምክንያቶች በፍጹም ተነጥለው ሊታዩ አይችሉም።

በመጀመሪያ የገበሬውን ሁኔታ እንመልከት። በህዝብ የመግዛት ኃይል ማነስና ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ ባህል አንፃር ገበሬው ለእህሉ ተመጣጣኝ ዋጋ እንደማያገኝ ይታወቃል። ገበሬው እራሱንና ቤተሰቡን እየበዘበዘ ለከተማው ህዝብ የሚያቀርበው እህል የሰፊው ህዝብ የሰውነቱ መጠገኛ ነው ማለት ይቻላል። ሰፊው ህዝብ ባለው ደካማ የመግዛት ኃይል ገበሬው ከፍተኛ ዋጋ ቢጠይቅ ሊገዛው የሚችል አይደለም። ስለዚህም በገበያ ላይ የሚቀርበው እህል አብዛኛውን ጊዜ በመግባባትና በመደራደር እንጂ ገበሬው ለስራ ጉልበቱ ፣ ለማረሻያ መሳሪያዎችና ለበሬው ያወጣውን ወጪ በማስላትና ትንሽ ትርፍ አክሎበት አይደለም እህሉን የሚሸጠው። ይሁ ሁኔታ ሊሻሻል የሚችለው የሰፊው ህዝብ የመግዛት ኃይል ሲጨምርና ገበሬውም ወጪውን ሲያሰላ ብቻ ነው። ይሁንና የእርሻን ውጤት በአቅራቢና በጠያቂ መሀከል በሚደረግ የገበያ ልውውጥ ዋጋን መደንገግ እንደማይቻል ፣ ስለዚህም ገበሬው የተወሰነ ተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዳለበት የታወቃና በአውሮፓ አንድነት ገበያ ውስጥ የሚሰራበት ዘዴ ነው።በዚህም ምክንያት ወደ ፊት ገበሬው ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ ከተፈለገ የመንግስት ድጎማ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል ማለት ነው። ገዝቶ የሚጠቀመው ህዝብ እንዳይበደል በምግብ ላይ የሚጫነው የተዘዋዋሪ ቀረጥ በጣም ዝቅ ማለት አለበት።

ይህ በእንደዚህ እንዳለ ባለፉት ዐመታት አንዳንዶች እንደሚሉት ገበሬው የተወሳሰበ አስተሳሰብ እያዳበረ እንደመጣና ከበፊቱ የተሻለ ኢንፎርሚሽን እንዳለው ስለዚህም የገበያውን ሁኔታ እየተጠባበቀ ምርቱን እንደሚሸጥ ይነገራል። ምናልባት ይህ ትንሽ እውነትን ያዘለ ነው ብሎ መቀበል ብንችልም ማራጋገጥ የሚቻለው በቦታው ተገኝቶ ጥናት ሲካሄድ ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ ገበሬውም ሆነ ነጋዴው ከአስር ዐመት በፊት ካለው ሁኔታ ባስተሳሰባቸው ተለውጠዋል። ይህ ደግሞ ገበያ ካለስርዓት ሊካሄድ የሚችል ልውውጥ ነው ተብሎ በሚወሰድበት አገር ገበሬውና ነጋዴው ህብረተሰቡ መግዛት ከሚችለው በላይ ዋጋ ሊጠይቁ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል። ይህም ሆኖ ነጋዴውንም ሆነ ገበሬውን መወንጀል በፍጹም አይቻልም። ምክንያቱም እንደዚህ ዐይነት ሁኔታ እንዳይፈጠር መንግስት ግዴታና ኃላፊነት ስላለበት ቀድሞ መውሰድ ያለበትን እርምጃ ማዘጋጀት አለበት። በየዐመቱ ለህዝብ የሚቀርበውን የእህል መጠን መቆጣጠር አለበት። ይህንን ትተን ሌሎች ነገሮችን ስንዳስስ በመጀመሪያ ደረጃ ከመንግስት ጋር የተያያዙ ድርጅቶች ራሳቸው ለእህል ዋጋ መናር ተጠያቂ እንደሆኑ ይታወቃል። እንደ ሰሊጥና አንዳንድ ስትራቴጂክ እህሎችን እየገዙ በአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ከመንግስት ጋር የተቆራኙ ኩባናያዎች ናቸው። ለምሳሌ እንደ ሰሊጥ ያለው ለዘይት የሚያገለግል የቅባት እህል በኢህአዴግ ቁጥጥር ሳር እንዳለና ወደ ውጭ ጥሬውን እንደሚላክ ይታወቃል። በአንፃሩ ግን አገሪቱ ከማሌዢያ ለጤንነት የማይስማማ ዘይት እያስመጣች በገበያ ላይ ይሸጣል። እንደዚህ ዐይነቱ የተዘበራረቀና የግብር ውጣ አስራር ባለበት አገር ውስጥ በተመጣጣኝ ዋጋ እህልም ሆነ ሌሎች ለምግብ የሚያገለግሉ ነገሮችን ማቅረብ በፍጹም አይቻልም። ከዚህ በተረፈ የመመላለሻ ኩባንያዎችን የሚቆጣጠረው ራሱ መንግስት ስለሆነ በእህል ዋጋ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል። ይህ በዚህ እንዳለ በመመላለሻ እጥረት ምክንያት ከመሚረተው ምርት ውስጥ 25% ብቻ ገበያ ላይ ቀርቦ ይሸጣል። ነገሩ ውስብስብ ነው ማለት ነው። ይህንን የተረዳች አንድ አሜሪካ አገር የተማረች ኢትዮጵያዊት ኢኮኖሚስት ገበሬው የተሻለ ኢንፎረሜሺን እንዲያገኝ ሀያ የሚጠጉ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በማቋቋም የእህል ገበያ (commodity market) ለመመስረት ሽር ጉድ እያለች ነው። ይህ ጉዳይ የቱን ያህል የሰፊውን ህዝብ የመግዛት ኃይልም ግምት ውስጥ እንዳስገባ ማወቅ አይቻልም።  በሌላ ወገን ግን ይህ ዐይነቱ እርምጃ ከሌሎች መሰረታዊ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። ቀደም ብለው ሊፈቱ የሚችሉ የፖለቲካና የኢንስቲቱሽን ጉዳዮች አሉ።

እነዚህ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው አገሪቱ የግሎባል ፕለየረስ መጫወቻ ከሆነች ወዲህ በአኗኗር ስልቱ እየተለወጠ የመጣ ልዩ የህብረተሰብ ክፍል ብቅ ብሏል። ይህ በጣም በገንዘብ የናጠጠ የህብረተሰብ ክፍል በተለይም በከተማ ውስጥ የሚኖረውን ሰፊውን ህዝብ ኑሮ እያናጋው እንደመጣ ግልጽ ነው። ይህ ልዩ ሁኔታ በመስኮውና አሁን ብቅ ብቅ ባሉት በዘይት በናጠጡ ከተሞች የሚታይ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠርን ህዝብ ያማረረ የኑሮ ሁኔታ ለውጥ ነው። ከውሃ ጀምሮ እስከ መብራት ድረስ ፣ ከከተማ ቦታዎች አንስቶ እስከ መኖሪያ ቤቶች ድረስ በዚህ አዲስ መጤ የህብረተሰብ ክፍል ቁጥጥር ስር እየወደቀ በመምጣቱ ሰፊው ህዝብ በኑሮው እየተገፋና በተለይም እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ከቆሻሻ ቦታዎች እየለቀመ ራሱንና ቤተሰቡን የሚመግብ ህዝብ ጥቂት እንዳይለ በገሀድ ይታወቃል። በሌላ አነጋገር ፣ ይህ አዲስ ቀበጥ የህብረተሰብ ክፍል ያመጣው የኑሮ ለውጥና የሚያገኘው ከፍተኛ ገቢ ለዋጋ መናር ዐይነተኛ ምክንያት ሆኗል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የምግብ ቤቶች ዋጋቸውን የሚተምኑት ከዚህ አዲስ ሊከፍል ከሚችል የመግዛት ኃይል ካለው የህብረተሰብ ክፍል በመነሳት ስለሆነ ነው። በተጨማሪም በአዲስ አበባ የተሰገሰገው ከአራት መቶ በላይ የሚቆጠረው የተራድዖ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ብዙ ሺህ ዶላር እያገኘ የሚሰራውና የሚኖረው የውጭ አገር ዜጋ ለኑሮ ውድነት ምክንያት ሊሆን ችሏል። ይህ ዐይነቱ በኒዎ ሊበራል የኢኮኖሚክ ፖሊሲ የተፈጠረ የህብረተሰብ ክፍል ለዚህ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ለህብረተሰቡ ባህል መናጋት ጠንቅ እየሆነ መጥቷል ማለት ይቻላል። ከዚህ በተረፈ ከሱዳን ወደ ጎንደር እየዘለቀ የሚመጣው አዲስ የዘይት ቱጃር ፣ ካለምንም ቁጥጥር ወደ አረብ አገሮች እየተጋዘ የሚሄደው ፍራፍሬ ፣ እህልና ከብት በህዝቡ ላይ ትልቅ ጫና ጥሏል ማለት ይቻላል። በዚህ ምክንያት ቀድሞ እንደ ልብ የሚገኘው ፍራፍሬ ሁሉ ገበያ ላይ ማግኘት የማይቻልበት ሁኔታ እንዲፈጠር እያደረገ ነው። በአንፃሩ ግን እንደዚያ አቮካዶ በብዛት በሚመረትበት አገር ፣ አገሪቱ የተገላቢጦሽ ከቻይና ታስመጣለች። በዚህ ምክንያት ጠቅላላው የህብረተሰብ ክፍል ኑሮ በመናጋት ሰፊው ህዝብ ባለው መጠነኛ ገቢ ገዝቶ ራሱን ሊመግብ የማይችልበት ሁኔታ ተከስቷል። ስለሆነም አንድ ኪሎ ሽንኩርት ሰባት የኢትዮጵያ ብር ያወጣል። አንድ ኪሎ ነጭ ሽንኩርት አስራ አራት የኢትዮጵያ ብር ያወጣል። አንድ ኪሎ ቅቤ አርባ የኢትዮጵያ ብር ያወጣል። አንድ ኩንታል ጤፍ እንደያይነቱ ከ370 እስከ 540 የኢትዮጵያ ብር ያወጣል። ሶስት መቶ ግራም የማይደርስ ክትፎ ወደ ሃምሳ የኢትዮጵያ ብር ይደርሳል። እንደዚህ እያልን ያለውን የኑሮ ውድነት መዘርዘር እንችላለን።

ከዚህ በተረፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ በቻይናና በህንድ የተከሰተው የአመጋገብ ባህልና አዲስ የመግዛት ኃይል እንደ ስንዴ ፣ እንደበቆሎና ሌሎች የእህል ዐይነቶችን ዋጋ ወደ ሰማይ እንዲተኮሱ እያደረገ ነው። በዚህ ላይ የነዳጅ ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ መሄድ በተለይም የኢንዱስትሪ አገር ገበሬዎችን የምርት ዋጋ እንዲናር እያደረገው ነው። የነዳጅ ዋጋ መጨመር በበለተኛው ህዝብ ላይ ካልሆነ በስተቀር በአገራችን ገበሬ ላይ ለማምረቻ ዋጋ በቀጥታ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በተረፈ በመንግስትም ሆነ በአንዳንድ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ለዋጋ መጨመር የሚሰጥ ምክንያት አለ። ይኸውም ኢኮኖሚው ከሚችለው በላይ የሚሽከረከረው ገንዘብ ለዋጋ መናር ምክንያት ሆኗል የሚል ነው። ይህ ከአስራሰባተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲያከራክር የቆየ ቲዎሪ እስካሁን ድረስ እንደ ዕውነት ተወስዶ ለዋጋ ግሽበት እንደምክንያት ይቆጠራል። ይህ ዐይነቱ የሞኔታሪስቶች ቲዎሪ በቀጥታ ለዋጋ መናር ተጠያቂነት ሊኖረው እንደማይችል በተለይም የማርክሲስት ኢኮኖሚስቶችና ጥንታዊ የሚባሉ ኢኮኖሚስቶች ያረጋግጣሉ። በሌላ ወገን ግን የአንድ አገር ህዝብ ተጨባጭ ደሞዝ እያደገ በሚሄድበት ወቅት በሚፈጠረው ተጨማሪ ጥያቄ መጠነኛ የዋጋ መናርን እንደሚያስከትል ግልጽ ነው። ያም ሆነ ይህ በአገራችን ብዙ ገንዘብ ስለሚሽከረከር ነው ዋጋ ሊወደድ የቻለው የሚለው ቦታ ሊኖረው አይችልም።እንደዚህ ብለን የምንቀበል ከሆነ የህዝብ ገቢ እያደገ መጥቷል ማለታችን ነው። ተጨባጩ ሁኔታ ግን ይህ እንዳልሆነና አብዛኛው ህዝብ በገንዘብ እጦት እንደሚሰቃይ ነው የሚታወቀው። በሌላ ወገን ግን ከአንድ ዐመት ተኩል ጀምሮ ዕውነተኛ ያልሆነ ገንዘብ ታትሞ በኢኮኖሚው ውስጥ እንደሚሽከረከር ከኢኮኖሚስ ጋር ዕውውቅ ያላቸውና ዕውነተኛውን ብር ትክክል ካልሆነው መለየት ከሚችሉ ሲነገር ተሰምቷል። አሁን ባለው የሀይ ቴክ ዘመን የተሳሳተ ገንዘብ ማተም ቀላል የሆነውን ያህል በዚያው መጠንም ለቁጥጥር የሚያመቹ መሳሪያዎች ተዘጋጅተው ተቀምጠዋል። ይህንን በተመለከተ መንግስት የቱን ያህል ዝግጅት ያድርግ አያድርግ ማወቅ የሚቻል ነገር የለም። ማለት የሚቻለው እስካሁን መቆየቱ ግን የሚያደናግር ሁኔታን እየፈጠረ ነው።

ያም ተባለ ይህ ፣ ለዋጋ ግሽበት አስር ምክንያቶቹ ቢደረደሩም አንድ መንግስት መሰረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ መረባረብ አለበት። ቢያንስ አንድ ህዝብ በቀን ሁለቴ ጠግቦ ሊበላና በየቀኑ ሳንቲም እየቆጠረ ሊኖር የማይችልበት ሁኔታ መፍጠር አለበት። ይህንን የማይችል መንግስትና ኢንስቲቱሽን እንደ መንግስት ሊቆጠሩ አይችሉም። እንደዚህ

ከቁጥጥር የወጣ ሁኔታ በሚፈጠርበት ገዜ አንድ ህዝብ ጩኸቱን የማሰማት መብት አለው። ማንኛውም መንግስት ይህንን ተፈጥሮአዊ በልቶ የማደርን መብት ሊነፈግ አይችልምና።

## አማራጭ ፖሊሲ

መንግስት የዋጋን ግሽበት ለመግታትና ዝቅ ለማድረግ የሚወስደው እርምጃ በፍጹም በቂ አይደሉም። ነጋዴውንም በማሰርና ሱቁን በመዝጋት ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት በፍጹም አይቻልም። ለዛሬው የኑሮ መመሰቃቀል ፣ ድህነትና የዋጋ መናር ዋናው ምክንያት ራሱ መንግስት የሚከተለው አገር አፍራሽ የኒዎ ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው። የመንግስቱ ባህርይና የሚከተላቸው የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል የሚያደልቡ ፖሊሲዎች ህብረተሰቡን መለወሻ እያሳጡት ነው። በዚህ ዐይነት የተዘበራረቀ ፖሊሲና ራሱ መንግስት ነጋዴም አስተዳዳሪም በሆነበት አገር ውስጥ ኢኮኖሚውን አሳድጎ ህብረተሰቡ የተደላደለ ኑሮ እንዲኖር ማድረግ በፍጹም አይቻልም። የዛሬው የኢኮኖሚ ድቀትና የህዝባችን ድህነት ካለው ጠቅላላ የፖለቲካ አወቃቀር ተነጥለው በፍጹም ሊታዩ አይችሉም። ይህ የሚያስመርር ኑሮ በገሀድ እየታየ መንግስትም ሆነ ካድሬዎቹ አገሪቱ በከፍተኛ እምርታ ላይ ነች ፣ ለውጥ እየታየባት ነው ፣ ለዚህም ካለ ኢህአዴግ ሌላ አስተማማኝ ኃይል ሊኖር አይችልም እያሉ ነጭ ውሸታቸውን ይነዛሉ። የዛሬው አገዛዝ በግልጽ የሚታዩ ነገሮችን በፍጹም ሊቀበል የተዘጋጀ ኃይል አይደለም።ስለሆነም አገዛዙም ሆነ እኛ ለአገር ተቆርቋሪ አገር ወዳዶች ልንወጣው የማንችለው ወጥመድ ውስጥ ገብተናል። አገዛዙ ማባበልና መለማመጥን በፍጹም አይወድም። ፖሊሲውንም ሊለውጥ በፍጹም ዝግጁ አይደለም። ተቃዋሚው ኃይል ደግሞ ተደራጅቶ ሁኔታውን ለመለወጥ ሲንቀሳቀስ አይታይም።

ለአገር ወዳዶች ያለው አማራጭ መንገድ በዚህ ዐይነት ፖሊሲ አንድ አገር እንደ አገርና እንደ ህብረተሰብ ልትኖር እንደማትችል በየጊዜው ለህዝብ ማሳወቅና አማራጭ መፍትሄ ማቅረብ ታሪካዊ ግዴታ ነው። በአገዛዙ ላይ የግዴታ ግፊት ማድረግና ዲሞክረሲያዊ የፖለቲካ ስርዓት እንዲፈጠር ሳይታክቱ መስራት የዚህም ሆነ የሚቀጥለው ትውልድ ታሪካዊ ግዴታ ነው።

በሌላ ወገን ተቃዋሚው ኃይል ለህዝብ መፍትሄ ለመስጠት የሚችል እንዲሆን አሁን ካለበት የርዕዮተ ዓለም ውዥንብር መላቀቅ አለበት። ከአገዛዙ የተሻለ አማራጭ ፖሊሲ እንዳለው በየዜና ማሰራጫዎቹ ሁሉ ድምጹን ማሰማት አለበት። በራሱ ኃይል ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ብቻ ታሪክን መስራት እንደሚችል ለህዝቡ ማረጋገጥ አለበት። የዓለም ኢኮኖሚ አወቃቀር እጅግ አወዛጋቢና የተመሰቃቀለ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ ጭንቀት ለመውጣት ወደ ሚያስችለው ብርሃንና ተስፋን ወደ ሚያመጣ ፍቱን መፍትሄ መሸጋገር አለበት። ዛሬ በተለይም አሜሪካ ውስጥ የተከሰተው የቤት አሰሪዎች ብድር ቀውስ ለብዙ ሰው ዐይኑን እየከፈተለት ነው። ይህንንም በሚመለከት የተገለጸላቸው አንዳንድ የአሜሪካን ኢኮኖሚስቶች አሜሪካን በዚህ መንገድ ወደፊት ልትቀጥልና ለሌሎች አገሮችም እንደ አርአያ ልትወሰድ እንደማትችል እየጠቆሙ ነው። በሌሎች አገሮችም የሚታየው ህብረተሰብአዊ ቀውስ የኒዎ ሊበራሊዝምንና የነፃ ንግድን ፍልስፍና መሰረት እያናጋው ነው። ባጭሩ በዚህ ርዕየተ ዓለም ምክንያት ብዙ ህብረተሰቦች እየተናጉ ናቸው። ጥቂት ኤሊቶች በመባለግ ህብረተሰብአዊ አመጽ እንዲከሰትና ተፈጥሮ እንድትዛባ እያደረጉ ነው። የአገራችንም ሁኔታ ከዚህ ውጭ ተነጥሎ በፍጹም ሊታይ አይችልም። ይህ ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ ብቻ ነው ወደ ትልቁ የህብረተሰብ ፕሮጀክት መሸጋገር የሚቻለው። ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰፈነው የስልጣኔ ቀውስ ግልጽ እስካልሆነ ድረስ ለህዝባችን የሚበጅ መፍትሄ ማቅረብ በፍጹም አይቻልም።

ከዚህ ስንነሳ ጠቅላላውን ህዝብ ለስራ የሚቀሰቅስ አጠቃላይ የህብረተሰብ ግንባታ ፖሊሲ መነደፍ አለበት። እንደ ኢትዮጵያ የመሰለን ትልቅ አገርና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣን ኢኮኖሚያዊና ህብረተሰብአዊ እንዲሁም ባህላዊ ችግርን እዚህና እዚያ በተንጠባጠበ ፕሮጀክት መፍታት አይቻልም። በታሪክ እንደ ተረጋገጠው ትልቅ አገር መመስረትና ችግርን መወጣት የሚቻለው ከትልቅ ሀሳብ ተነስቶ ህብረተሰብአዊ ፕሮጀክት ሲነደፍ ብቻ ነው። ቢያንስ ያለፈው የሁለት ሺህ አምስት መቶ ዐመት የሰው ልጅ ታሪክ የሚያረጋግጠው ይህንን ነው። ቀጫጫ ሃሳብ በተንሰራፋበትና ኒዎ ሊበራሊዝም አማራጭ እንደሌለው ፖሊሲ ተደርጎ በሚወሰድበት አገር ዕውነተኛ ለህዝብና ለትውልድ አለኝታ

**የሚሆን ታሪክ መስራት በፍጹም አይቻልም። በተጨማሪም አንድ ህዝብና ጥቂት ኤሊቶች በሆነው ባልሆነው በሚናቆሩበት አገር አስተሳሰብ ስለሚበታተን ኃይልን ሰብሰብ አድረጎ ቁምነገር መስራት አይቻልም። እንደሚባለው በአገራችን ያለው ችግር የካፒታል እጥረት ወይም የጥሬ ሀብት ችግር አይደለም። የኛ ችግር መናናቅ ፣ ስራን መናቅ ፣ኃይልን የሚበታትን ተንኮል መሸረብና ተስፋ ማሰቆረጥ ወዘተ... እንደባህል በመወሰዳቸው ለታሪካዊ ስራ እንቅፋት ሆነዋል። በዚህ ላይ በየጊዜው የሚካሄደው የገዢዎች የፖለቲካ ሸወዳ አገርን ወደ ማፈራረስ ደርሷል። የኛ ትልቁ ችግር ይህንን ለመገንዘብ ያለመቻል ነው።**

**ይህ ግልጽ ከሆነ ትንሽ ጊዜ ቢቆይም የዛሬው አገዛዝ ካተረማመሰው ኢኮኖሚ ተላቀን ነፃና የተደላደለች እንዲሁም ለእያንዳንዱ ዜጋ የምታመች አገር መመስረት ይቻላል። ለዚህ ሁሉ ግን ራስን መጠየቅ ፣ መደማመጥና መግባባት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። ይህ ሁኔታ በሌለበት ማህበረሰብ ውስጥ ጥሩ ሃሳብን ተግባራዊ ማድረግ ከቶውንም አይቻልም። ከአመጽ ይልቅ ሃሳብ ወደ ሚያሸንፍበት መድረክ ከተሸጋገርን ረሀብን ማስወገድና ለህዝባችን የሚያስፈልገውን የቀን ተቀን ምግብ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ታሪክንም መስራት ይቻላል።**

**ፈቃዱ በቀለ**